# ርምጃ አንድ

ብ. ነጋሽ 02-01-18

መብትና ነጻነቱን ያወቀና የኖረበት እንዲሁም ዴሞክራሲንና ልማትን የቀመሰ ህዝብ ከቶም ወደ ኋላ አይመለስም። እነዚህን በእጁ የገቡ እሴቶች አያስነካም። አለማስነካት ብቻ አይደለም፤ ሁሌም ተጨማሪ ይፈልጋል። ፍጹም ዴሞክራሲን፣ በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ላይ ያለንና በተሻለ ህይወት የሚገለጽ ልማትን ይጠይቃል። እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰን ህዝብ መጨቆን አይቻልም። እንኳን ጨቋኝ መንግስት ቀርፋፋ መንግስትም እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰን ህዝብን አይመጥንም። በማያቋርጥ ለውጥ ላይ ያለውን የህዝብን የዴሞክራሲና የልማት ጥያቄ መመለስ የሚችል ንቁና ፈጣን መንግስት ነው የሚመጥነው። መንግስቱ ከተንቀራፈፈበት ህዝቡ ውክልናውን ማንሳቱ አይቀሬ ይሆናል።

አሁን የኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነጻነቱን የራሱ አድርጓል። በዴሞክራሲ ውስጥ አልፏል። ልማትን ቀምሷል። እነዚህን አያስነካም። ካሁን በኋላ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በሚኖሩበት መሬት ላይ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር - በተወካዮቻቻው የመተዳደር፣ በቋንቋቸው የመስራት፣ ባህላቸውን የማሳደግ፣ ታሪካቸውን የመንከባከብ፣ በፌደራል መንግስት ውስጥ ውክልና የማገኘት መብትና ነጻነታቸውን አያስነኩም።

ይህ ብቻ አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ አሁን ተጨማሪ ልማትና ዴሞክራሲ የሚፈልገበት ደረጃ ላይ ነው። የመንገድ፣ የኤሌትሪክ፣ የቴሌኮሚዩኒኬሽን ወዘተ መሰረተ ልማት ይፈልጋል። ስራ አጥነትን ተሸክሞ መዝለቅ አይፈልግም። የተሟላ የጤናና የትምህርት አገልግሎት ይሻል። በአጠቃላይ *አምጣ!* የሚል ህዝብ ተፈጥሯል።

ታዲያ፣ የኢፌዴሪ መንግስት፣ የየክልሉን መንግስታት ጨምሮ ባለፉት ሃያ ዓመታት በሃገሪቱ ታሪክ ያልነበረ ዴሞክራሲን ማስፈንና ልማትን ማምጣት መቻላቸው እውነት ቢሆንም፣ የህዝቡን የፍላጎት እድገት ተከተለው እርካታ መፍጠር ላይ ግን መንቀራፈፍ ታይቶባቸዋል። አሁን የኢትዮጵያ ህዝብ ትምህርት ቤትና የጤና ተቋም ሳይኖረው መኖር አይፈቅድም። አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲኖረው፣ ሁለተኛ ደረጃ ይፈልጋል፤ ሁለተኛ ደረጃ ሲኖረው ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ይፈልጋል። ጤና ጣቢያ ሲኖረው ሆስፒታል ይጠይቃል። የጠጠር መንገድ ሲኖረው መንገዱ አስፋልት እንዲሆንለት ይፈልጋል። የኤሌትሪክ

ሃይል ሲያገኝ፣ ከመብራት አልፎ ከፍተኛ ጉልበት ያለው ሃይል እንዲኖረው ይፈልጋል። የቴሌፎን አገልግሎት ሲያገኝ፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ይጠይቃል። የልማት ፍላጎቱ አይቋረጥም። የዚህ አይነት ህዝብ የተፈጠረው በኢፌዴሪ መንግስትና ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ቢሆኑም፣ ራሳቸው በፈጠሩት የህዝብ ፍላጎት እድገት ፍጥነት ልክ መጓዝ ግን አልቻሉም።

የህዝቡን የሚያቋርጥ የልማት ፍላጎት ማሟላት የሚያስችል አመራር መስጠት ካለመቻል በተጨማሪ ከራይ ሰብሳቢነት ገብቷቸው ከህዝብ ጋር የተፋጠጡበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። በሁለት ዓመት ይጠናቀቃል ተብለው የሚጀመሩ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች፣ የኢኮኖሚ የማህበራዊ ልማት ፕሮጀክቶች በሁለተኛው ዓመት ላይ የተመደበላቸውን ባጀት ቅርጥፈው ጨርሰው በጀምር የሚቀሩበት ሁኔታ የተለመደ እየሆነ ሆኗል። ተገንብተው የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች በተጠናቀቁ ማግስት ፈራርሰው አገልግሎት መስጠት የሚያችሉበት ሁኔታን መመልከት የተለመደ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን የመልካም አስተዳደሩና የፍትህ እጦቱ፣ የሙሴት ወረራው፣ የተበዳይ አቤቱታ ሰሚ ማጣቱት ወዘተ ህዝብ መንግስት ላይ አመኔታ እንዲያጣ አድርጓል።

ልማቱና ዴሞክራሲ የቀመሰን ህዝብ በዚህ ሁኔታ ማስተዳደር ስለሚይቻል፣ ህዝብ መንግስት ላይ ያለውን ቅሬታ በተቃወሞ አሳወቋል። መንግስትና ገዢው ፓርቲ አስቀድመውም ይህን አዝማሚያ አወቀውት ነበር። የችግሩ ምንጭ ወስጣዊ መሆኑን፣ ይህ ወስጣዊ ችግር ስርአቱንና ሃገሪቱን ለወጫዊ ጥቃት ሚጋለጡ አይቀሬ መሆኑን ተረድተው የህዝብን ብሶት አዳምጠው ፈጣን ምላሽ ለመስጠት በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ጀምረዋል።

በዚህ መሰረት በፌደራልና በክልል መንግስታ አዳስ ካቢኔ እንዲዋቀር ተደርጓል። የፖለቲካ ምህዳሩን ወቅቱ በሚጠይቀው ልክ ለማስፋት ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በተለያዩ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ እንዲሁም በስራ ላይ ያሉ አዋጆችን ለማስተካከል ድርድር ተጀምሯል። ይሁን እንጂ ቀደሞ የነበሩት ስር የሰደዱ የገዢው ፓርቲ ኢህአዴግና የመንግስት ችግሮች ላይ በየአካባቢው የተፈጠሩ የእርስ በርስ ግጭቶችና ሌሎች ወጩዊ ሁኔታዎች ታክለው በታሰበው ልክ በተጨባጭ የሚታይ ለወጥ ማምጣት ያልተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ገዢው ፓርቲ አሁንም ለህዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ራሱን ለማስተካከል ወስኖ ግምገማ አካሂዷል።

በቅርቡ የተካሄደውና በርካታ ወሳኔዎች የተላለፉበት የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ግምገማ የዚህ ማሳያ ነው። ግምገማው እንዳበቃ የኢህአዴግ አራት እህትማማች ድርጅቶች አመራሮች በጋራ የግምገማውን ሂደት፣ የደረሱበትን መግባባትና ወሳኔዎቻቸውን የተመለከተ መግለጫ ሰጥተዋል። ከተላለፉ ወሳኔዎች መሃከል ሃገራዊ መግባባት መፍጠርና ሃገራዊ አንድነትን መገንባት የሚያስችሉት በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ከእነዚህ መሃከል አንዱ በወንጀል ተጠርጥረው ክስ የተመሰረተባቸውና በጥፋተኝነት የተፈረደባቸውን የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና ሌሎች ግለሰቦች ክስ በማቋረጥና በይቅርታ ነጻ እንዲወጡ ሚደረግ ነው። ይህ እርምጃ በወንጀል የተጠረጠሩትና በጥፋተኝነት የተፈረደባቸው ፖለቲከኞች የሚመሯቸው ፓርቲዎች ደጋፊዎች በመንግስትና በገዢው ፓርቲ ላይ ያደረባቸውን ጥርጣሬ የመግፈፍ አቅም አለው። ፓርቲዎቹ ከመንግስት ጋር በሚያደርጉት ወይይትና ድርድር የተሳትፎ አቅማቸውንም የሚያዳብርበት ሁኔታም አለ።

ይህ ደግሞ በተለያዩ አመለካካት ተከታይ ዜጎችና ቡድኖች መሃከል እንዲሁም በመንግስትና በህዝብ መሃከል መተማመንና ሃገራዊ መግበባት መፍጠር ያስችላል ተብሎ ይታመናል። በዚህ መሰረት የፌደራል መንግስት፤ የደቡብ ብሄሮች፣

ብሄረሰቦችና ህዝቦች፤ የኦሮሚያና የአማራ ክልሎች በክስ ሂደት ላይ የነበሩና ፍርደኛ እስረኞችን ነጻ አሰናብተዋል። በፌደራል መንግስት በኩል እስካሁን የተለቀቁት በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ሲሆኑ፣ ፍርደኞቹ ህግ በሚፈቅደው መሰረት እየተጣሩ እንደሚለቀቁ ጠቅላይ አቃቤ ህግ አስታውቋል።

ይህ እርምጃ የመጀመሪያወና መንግስት ወሳኔዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ ያለወን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው። በቀጣይ የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያሳለፋቸው ሌሎች ወሳኔዎችም ተግባራዊ ይደረጋሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ከበርካቶቹ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወሳኔዎች መካከል በመድብለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታ ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን ከሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶችና ከህዝቡ ጋር በመሆን ለማቃለል ያግዛሉ በሚል ያሳለፋቸው ወሳኔዎች ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸው ናቸው። በዚህ ወሳኔ መሰረት ምሁራንና የሲቪክ ማህበራት ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታና የዴሞክራሲ ምህዳሩን ለማስፋት ተገቢ ሚናቸወን የሚጫወቱበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር የሚያስችል እርምጃ ይወሰዳል።

በተጨማሪም፤ የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሃገራዊ አንድነትን ለማጠናከር የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎችን ከህዝቡና ከመንግሥት ጋር በመሆን ማከናወን እንደሚገባ አቅጣጫ አስቀምጧል። የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ባጸደቁት ህገመንግስት መሰረት ራሳቸወን በራሳቸው የሚያስተዳደሩበት መንግስታዊ መዋቅር ካደራጁ 23 ዓመታት ተቆጥረዋል። ይህ የዘመናት የህዝብ ትግል ወጤት የሆነ ታሪካዊ ድል ነው። ይሁን እንጂ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሃገራዊ አንድነታቸወን ማጠናከር የሚችሉበትን ተግባር ማከናወን ላይ ክፈተት ታይቷል። በዚህ ምክንያት ልዩነቶች እየሰፉ፣ ልዩነቶች በሰፋበት ልክ ሃገራዊ አንድነት እየላላ የመጣበት አዝማሚያ ታይቷል። ሃገራዊ አንድነትን የማጠናከር እርምጃ መወሰድ የሚያስችል አቅጣጫ ማስቀመጥ ያስፈለገው ለዚህ ነው። በዚህ ረገድ ጅምር ስራዎች ቢኖሩም በቀጣይነት አጥጋቢና ሁሉን አቀፍ በሆነ መልክ ይተገበራል ተብሎ ይጠበቃል።

በጽሁፉ መግቢያ ላይ እንደተመለከተወ፣ የፌደራልም ሆነ ይክልል መንግስታት የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት የህዝቡን የልማት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ፍላጎትና ጥያቄ ማርካት አልቻሉም። ይህ የሆነው መንግስታቱ ከህዝቡ ፍላጎት ጋር ጋር በፍጥነት እየተራመዱ የሚያቋርጠወን ፍላጎቱን የማሟላት አቅም በማጣታቸው፣ የህዝብ አገልጋይነት መንፈስ በማጣት ስልጣኑን ለግል ኑሮ ማደላደያ በማድረጋቸወና በከራይ ሰብሳቢነት ምክንያት ነው። የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በፌደራልም በክልልም ያለው ሲቪል ሰርቪስ ከመቼወም ጊዜ በበለጠ የአገልጋይነት መንፈስ የሕዝቡን ጥያቄዎች ለመመለስ እንዳረባረብ ማድረግ የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠር ቃል ገብቷል። ይህ እስካሁን ያለወን የህዝብ ቅሬታ በመሉ በማቃለል ተስፋ የሚፈጥር፣ በመንግስትና በህዝብ መካከል መተማመን መገንባት የሚያስችል ርምጃ ነው።

በአጠቃላይ፤ የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ካሳለፋቸው በርካታ ወሳኔዎች መካከል የፖለቲካ አመራሮችን የመፈታቱ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። ይህ ሌሎቹም ወሳኔዎች ተግባራዊ እንደሚደረጉ ያመለክታል። ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎቹም የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያሳለፋቸው ወሳኔዎች ተግባራዊ ይሆናሉ ተብሎ የጠበቃል። ወሳኔዎቹን ተግባራዊ ማድረግ የምርጫ ጉዳይ አይደለም። ተግባራዊ አለማድረግ የህዝብን ቁጣና ተቃወሞ በማባባስ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ሂደትን በሚደናቀፍ የሃገሪቱን ህልወናም አደጋ ላይ እስከመጣል ሊደርስ ይችላል። እናም እስረኞችን በመፍታት የተጀመረው ርምጃ በፍጥነትና ተጨባጭ ለወጥ ሊያመጣ በሚችልበት ሁኔታ መቀጠል አለበት። እስረኞቹን የመፈታቱን ተግባር፣ ርምጃ አንድ እንበለው። ርምጃ ሁለት፣ ሶስት . . . ይቀሩናል።